
# Explanation of The Meaning of Tagoot

# የጣዖት ትርጉም ማብራሪያ



በወጣቱ ተልዕኮ (በአህመድ የሱፍ)

**Presented by Youth-Mission Online Amharic Islamic Books publishing.**

# Explanation of The Meaning of Tagoot

# የጣዖት ትርጉም ማብራሪያ

**በኢማም ሙጀዲድ ሙሐመድ ቢን አብዲል ዋሃብ**

**ትርጉም በአህመድ የሱፍ**

**All right reserved**

**© የወጣቱ ተልዕኮ**

**የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008**

**ሰሜን ወሎ ወልዲያ**

**ahmedyesuf29@gmail.com**

**+251927790323**

**http://youth-mission.mobie.in**

ይህ መፅሐፍ የተተረጎመው ከመጀመሪያው የአል ኢባና የግንቦት 2003 እትም ከሆነው የኦንላይን Ebook ነው። www.al.ibanah.com

ይህች በእጃችሁ ላይ ያለችው መፅሐፍ ከሙሐመድ ኢብን አብዱል ወሃብ "ማዕነቱ ጣጉኡት" ከሚለው ፅሁፋቸው እና ከዶ/ር ሙሐመድ ቢን አብዱ ረህማን አልኩመይስ ማብራሪያ የተተረጎመ ሲሆን በዚች ፅሁፍ ቃል በቃል ለመተርጎም የሞከርኩ ሲሆን ከርእሶቹ ጋርም ተዛማጅናቸው ያልኩቸውን እና የበለጠ ለማርራራት ይረዳሉ ያልኳቸውን ሃሳቦችና ቃላት ለማካተት ሞክሪያለሁ። እንዲሁም አንዳንድ ቦታ ላይ የአረፍተ ነገር መደጋገም ለማስቀረት ሃሳቡን ጠቅለል ባለመልኩ ለመግለፅ ሞክሪያለሁ።

## በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

## ክፍል አንድ

## በሰው ልጆች ላይ የተደነገገው የመጀመሪያው ግዴታ

አሏህ ይዘንልህና እወቅ! አሏህ በአደም ልጆች ላይ ግዴታ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር በጣኦቶች መካድ እና በአሏህ ማመን ነው። ለዚህ ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

**=<({አል-ቁርአን 16:36})>=**

**وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِى كُلِّ أُمَّةٍ۬ رَّسُولاً أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَ**

**{36} በእርግጥም በእያንዳንዱ ህዝብ መሃል አሏህን ተገዙ ከጣኦታቶችም ራቁ በማለት መልእክተኛን ልከናል።**

## ማብራሪያ

**<u>የቃላት ፍች</u>**

- ፈረዶ__ ግዴታ የሆነ
- ጣጉኡት የሚለው ቃል ጣጋአ ከሚለው ስረወቃል የተመሰረተ ሲሆን ትርጉሙም መጣስ ወይም ድንበር ማለፍ ማለት ነው።

ሸኹም አሏህ ስራቸውን ይውደድላቸውና ይችን አንስ ያለች ፅሑፍ ያዘጋጁት አሏህ በሰው ልጆች ላይ መጀመሪያ ግዴታ ያደረገውን ነገር በማብራራት ሲሆን ከአሏህ ንግግር ከሆነው ቁርአን ማስረጃዎችን በማስደገፍ ነበር። ይህ ግዴታ በጣኦታቶች መካድና በአሏህ ማመን ነው። አሏሁ አዘወጀል በሱረቱ ነህል አንቀፅ 36 ላይ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 16:36})>=**

وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِى كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولًا أَنِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَٱجْتَنِبُوا۟ ٱلطَّٰغُوتَ

**{36} በእርግጥም በእያንዳንዱ ህዝብ መሃል አሏህን ተገዙ ከጣኦታትም ራቁ በማለት መልዕክተኛን ልከናል።**

እናም የመጀመሪያው ነገር መጣል ፣ አለመቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ሲሆን ይህም በጣኦቶች ከአሏህ ውጭ በሚመለኩ ነገሮች መካድ ነው። ይህ ማንኛውንም የውሸት አማልክቶችን ሁሉ ያጠቃልላል። ለምሳሌ ዛፍ ፣ ድንጋይ ፣ ፀሃይ ፣ ጨረቃ ፣ መላኢካ ፣ ሰው እነዚህና ሌሎችም። እነዚህ ነገሮች ከአሏህ ውጭ የመመለክ መብት የላቸውም። ምክኒያቱም በዚህ ፍጥረተ አለም ላይ በምንም ጉዳይ ላይ የማዘዝ ብቃቱ የላቸውምና።

ከዚህ ብኋላ የሚመጣው ሃይማኖትን በቅንነት ወይም አጥርቶ (በኢህላስ) ለአሏህ ብቻ ምድረግ ፣ እሱን ብቻ መገዛት ፣ ከሌሎች በመነጠል መብቱን ማረጋገጥ ነው። ይህ ግዴታ በጣኦታቶች የመካድ እና በአሏህ የማመን ግዴታ ሲሆን የላኢላሃ ኢለሏህ ትርጉም ነው። ላኢላሃ_ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ የለም። ኢለሏህ_ ከአሏህ በቀር። በእርግጥም ይህ ውድቅ የማድረግና የማረጋገጥ መርህ ነው። ላኢላሃ የሚላው ከአሏህ ውጭ የሚመለኩ ነገሮችን በሙሉ ውድቅ ማድረግና አለመቀበል ሲሆን ኢለሏህ የሚለው ደግሞ ሊመለክ የሚገባው ወይም

የመመለክ ብቸኛ መብት ያለው አሏህ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጥ ነው።

በዚህም የመጀመሪያው በሰው ልጆች ላይ ግዴታ የሆነው ነገር በጣኦቶች መካድ እና በአሏህ ማመን እንደሆነ ግልፅ ቢሆንም አንዳንድ አፈንጋጭ ቡድኖች ግን ከዚህ ግዴታ ይልቅ ማሰብና መመራመር አቅል ይቀድማል ብለው ያምናሉ።

## ማጠቃለያ

1. በአንድ የአሏህ ባርያ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ግዴታ የሆነበት በጣኦታቶች መካድ እና በአሏህ ማመን ነው።

2. ጣኦት ማለት ከአሏህ ውጭ የሚመለክ ማንኛውም ነገር ነው።

3. በሰው ልጆች ላይ የተደነገገው የመጀመሪያው ግዴታ አሏህ እንደገለፀው በጣኦት መካድና በአሏህ ማመን ቢሆንም አንዳንድ አፈንጋጭ ቡድኖች ግን ከዚህ ግዴታ ይልቅ በመጀመሪያ ማሰብና መመራመር ይቀድማል ይላሉ።

## ጥያቄና መልስ

1. በሰው ልጆች ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ግዴታ የሆነው ነገር ምንድ ነው? ከማስረጃ ጋር መልስ

2. ጣኦት የሚለው ቃል ትርጉም ወይም ፍች ምንድነው?

3. የላኢላሃ ኢለሏህ ትርጉም አብራራ? ውድቅ ማድረግና ማፅደቅ ሲባል ምን እንደሆነ አያይዘህ አስረዳ?

4. በሰው ልጆች ላይ ግዴታ በሆነው ነገር የማያምኑ እነማን ናቸው? እምነታቸውስ ምንድነው?

# ክፍል ሁለት

## በጣኦታቶች የመካድ እና በአሏህ የማመን ትርጉም

በጣኦታቶች መካድ ማለት ከአሏህ ውጭ ያሉ ነገሮችን ማምለክ ከንቱነት እንደሆነ ማመን ሲሆን ሆኖም ይህን ከማድረግ ፈፅሞ መራቅ እና መጥላት እንዲሁም ጣዖት የሚያመልኩ ሰዎችን መጥላት ጭምር ነው። በአሏህ የማመን ትርጉም ከማንኛውም ነገር ተነጥሎ በብቸኝነት ሊመለክ የሚገባው ጌታ አሏህ እንደሆነ ማመን ሲሆን ከአሏህ ውጭ በሚመለኩ ነገሮች ከካዱና ካልተቀበሉ ቡኋላ ሁሉንም የአምልኮት ተግባራት አጥርቶ (በኢህላስ) ለአሏህ ብቻ ማድረግን እንዲሁም የሽርክ ሰዎችን በመጥላትና ጠላትነትን በማሳየት ፣ የኢህላስ ሰዎችን መውደድና መጎዳኘት ያጠቃልላል። ይህ የኢብራሂም ሃይማኖት ሲሆን ከዚህ ማፈግፈግ ወይም መሸሽ እራስን ማቄል(ማሞኘት) ነው። ይህ አሏህ በንግግሩ ያሳወቀን ምርጥ ምሳሌ ነው።

**=<({አል-ቁርአን 60:4})>=**

**قَدۡ كَانَتۡ لَكُمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٌ ۖ فِيٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ إِذۡ قَالُواْ لِقَوۡمِهِمۡ إِ**
**نَّا بُرَءَٰٓؤُاْ مِنكُمۡ وَمِمَّا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ كَفَرۡنَا بِكُمۡ وَبَدَا بَيۡنَنَا وَبَيۡنَكُمُ ٱلۡعَ**
**دَٰوَةُ وَٱلۡبَغۡضَآءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ وَحۡدَهُۥٓ**

**{4} በእርግጥ በኢብራሂምና ከእሱ ጋር በነበሩት(ምዕመናን) ምርጥ ምሳሌ አለላችሁ። ለህዝቦቻቸው ባሉ ጊዜ፤ በእርግጥ እኛ ከእናንተና ከአሏህ ውጭ ከምታመልኩት ነገር የጠራን ነን። በእናንተ ካድን፤ በአሏህ እስከታምኑ ድረስ በእናንተና በእኛ መካከል ጥላቻና ጠብ ለዘላለም ተገለፀ።**

## ማብራሪያ

**<u>የቃላት ፍች</u>**

- ሳፊሃ_ እራስን ማሞኘት ወይም እራስን ማሳሳት
- ኡስዋ_ ምሳሌ ፣ አርአያ
- በደአ_ ተጀመረ ፣ ተገለፀ

ጣኡቶችን ውድቅ ማድረግ ወይም አለመቀበል እና በእነሱ ያለማመን መገለጫው ከአሏህ ውጭ የሆኑ ነገሮችን ማምለክ ሐሰትና ጥመት እንደሆነ ማመን ነው። አሏሁ አዘወጀል በሱረቱል ሐጅ አንቀፅ 62 ላይ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 22:62})>=**

وَأَنَّ مَا يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ هُوَ ٱلۡبَٰطِلِ

**{62} ከእሱ ውጭ የሚጣሩት (የሚያመልኩት ፣ የሚገዙት) እርሱ ባጢል(ውሸት) ነው።**

**እናም እንዲህ አይነቱን የአምልኮት ተግባራት መተውና መራቅ ወደ እነሱም አለመቅረብ ፣ ከአምልኮተ አሏህ ጋር ምንም ነገር አለመቀላቀል ነው። ምክኒያቱም አሏህ ከህደትንና ጣኡቶችን ማምለክ ይጠላል። አሏሁ አዘወጀል እንዲህ ይላል፡-**

**=<({አል-ቁርአን 39:7})>=**

**إِن تَكۡفُرُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنكُمۡۖ وَلَا يَرۡضَىٰ لِعِبَادِهِ ٱلۡكُفۡرَ**

**{7} ብትክዱ በእርግጥ አሏህ አይፈልጋችሁም፤ ለባሮቹም ክህደትን አይወድም።**

ይህ የጣዖት ሰዎችን በክህደት ላይ እንደሆኑ ማመን ፣ ከነሱ ጋር ጠላት መሆን ፣ እነሱ ጋር አለመመሳጠር ፣ ለነሱ ውዴታን አለማሳየት ፣ እነሱን አለመርዳት ያጠቃልላል። በአሏህ የማመን ትርጉም አሏህ ብቸኛው ጌታ ፣ ከሌሎች ተነጥሎ ሊመለክ የሚገባው ብቸኛው አምላክ እንደሆነ ማመን ነው። እናም ከአሏህ ውጭ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ አንድም ነገር የለም። አሏህም እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 22:62})>=**

**ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡحَقُّ**

**{62} ያ ምክኒያቱም አሏህ እርሱ እውነት ነው።**

ልክ እንደዚሁ የኢባዳ አይነቶች ሁሉ በኢህላስ ለአሏህ ብቻ ተብለው መሰራት ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ሶላት ፣ ፆም ፣ ዘካ ፣ ሐጅ ፣ ዱአ ፣ መሃላ ፣ መመካት ፣ ተስፋ ማድረግ ፣ ፍራቻ እና ሌሎችም። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ከአሏህ ውጭ ለሚመለኩ ነገሮች ከማድረግ ይልቅ ሙሉ በሙሉ አጥርቶ ለአሏህ ብቻ መደረግ አለባቸው። አሏህም እንዲህ ይላል፡-

**=<(⦃አል-ቁርአን 39:14⦄)>=**

## قُلِ ٱللَّهَ أَعۡبُدُ مُخۡلِصٗا لَّهُۥ دِينِي

**⦃14⦄ ለአሏህ ሃይማኖቴን ለእርሱ ያጠራሁ ሆኜ እገዛዋለሁ በል!**

ታዲያ እነዚህን አይነት የአምልኮት ተግባራት ከአሏህ ውጭ ላሉ ነገሮች ማድረግም ሆነ ሰዎችን ወደዚህ ማመላከት አይፈቀድም። ሆኖም በዚህ ተግባር ላይ የወደቀ ሽርክ ላይ ነው ማለት ነው።

በአሏህ ማመን ከሚካተቱ ነገሮች ውስጥ በኢህላስ እሱን የሚገዙትን የተውሂድ ሰዎችን መውደድ እና ከነሱም ጋር መወዳጀት ፣ እነሱን ማገዝና መርዳት ሲሆን ሙሽሪክ የሆኑ የአሏህን ጠላቶች መጥላት ፣ ከእነሱ ጋር አጋርነትን አለመፈለግ ፣ ከእነሱ ጋር ያለውን ቀረቤታ መተው ወይም ማቋረጥን ያጠቃልላል። ምክኒያቱም በጦበራኒና በአህመድ በተዘገበው ሐዲስ መሰረት የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ጠንካራው ኢማን ለአሏህ ብሎ መውደድ እና ለአሏህ ብሎ መጥላት ነው ብለዋል። አሏሁ አዘወጀል በሱረቱል በቀራ አንቀፅ 130 ላይ እንዲህ ብሏል፡-

**=<(⦃አል-ቁርአን 2:130⦄)>=**

## وَمَن يَرۡغَبُ عَن مِّلَّةِ إِبۡرَٰهِـۧمَ إِلَّا مَن سَفِهَ نَفۡسَهُۥ

**⦃130⦄ ከኢብራሂም መንገድ(ሃይማኖት) የሸሸ(ያፈገፈገ) ማን አለ እራሱን ያቄለ ቢሆን እንጅ?**

አሏህም ኢብራሂም(ዐ.ሰ) እና ተከታዮቹ በከሃዲያን ህዝቦቻቸው ላይ የወሰዱትን አቋም እና እኛም ልንከተለው ስለሚገባው ምርጥ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነግሮናል፡-

**=<({አል-ቁርአን 60:4})>=**

**قَدۡ كَانَتۡ لَكُمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ فِيٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ إِذۡ قَالُواْ لِقَوۡمِهِمۡ إِنَّا بُرَءَٰٓؤُاْ مِنكُمۡ وَمِمَّا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ كَفَرۡنَا بِكُمۡ وَبَدَا بَيۡنَنَا وَبَيۡنَكُمُ ٱلۡعَدَٰوَةُ وَٱلۡبَغۡضَآءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ وَحۡدَهُۥٓ**

**{4} በእርግጥ በኢብራሂምና ከእሱ ጋር በነበሩት(ምዕመናን) ምርጥ ምሳሌ አለላችሁ። ለህዝቦቻቸው ባሉ ጊዜ፤ በእርግጥ እኛ ከእናንተና ከአሏህ ውጭ ከምታመልኩት ነገር የጠራን ነን። በእናንተ ካድን፤ በአሏህ እስከታምኑ ድርስ በእናንተና በእኛ መካከል ጥላቻና ጠብ ለዘላለም ተገለፀ።**

እናም እራሳቸውን ከከሃዲያኖች ነፃ በማድረግ ከአሏህ ውጭ የሚያመልኩትንም ነገር ሆነ በእነሱ ካዱ፤ ኢባዳዎችን ከሌሎች ነጥለው ለአሏህ ብቻ እስኪያደርጉ ድረስም ጠላቶቻቸው እንደሆኑ ፣ ጥላቻቸው ለነሱ የነበራቸውን ፍቅርና ውዴታ እንዳቋረጠው ፣ በመካከላቸውም ጠብና ጥላቻ ለዘላለም እንደተገለፀ አወጁ።

## ማጠቃለያ

1. በጣዖታቶች የመካድ ትርጉም በነሱ ማመን ማለት ጥመትና ከንቱነት እንደሆነ ማመን ሲሆን ጣኦታቶችን ውድቅ ማድረግ ፣ አማኞችንም እንደ ከሃዲ መቁጠር እና ከእነሱም ጋር አለመወዳጀት ነው።

2. በአሏህ ማመን ኢባዳን በኢህላስ አጥርቶ ለአሏህ ብቻ ማድረግ ፣ የኢማን ሰዎችንም መውደድና ከእነሱ ጋር መወዳጀት ነው።

3. እነዚህ ሁለት መሰረታዊ ነገሮች የኢብራሂምን ሃይማኖት መሰረት ይፈጥራሉ።

## ጥያቄና መልስ

1. የኢብራሂም ሃይማኖት መሰረቱ ምንድነው?

2. በጣኦታቶች መካድ ማለት ምን እንደሆነ እጥር ምጥን ባለ መልኩ አብራራ?

3. በአሏህ ማመን እና አማኞችን በመውደድና ከእነሱ ጋር በመወዳጀት መካከል ግኑኝነት አለ?

## ክፍል ሶስት

## የጣኦት ትርጉምና ክፍሎቹ

ጣኦት የሚለው ቃል ጠቅለል ያለ ሲሆን ማንኛውም ከአሏህ ውጭ የሚመመለክ ፣ ሰዎች የሚከተሉት ፣ አሏህንና መልዕክተኛውን አለመታዘዝ በሆነ ነገር ላይ ሰዎች የሚታዘዙት ነገሮች በሙሉ እንደ ጣኦት ይቆጠራሉ። ጣጉኡት የሚለው ቃል ነጠላ ወይም አንድን ጣኦት የሚገልፅ ሲሆን ጠዋጊት ግን ብዛትን ገላጭ ነው። ሆኖም በጣም በርካታ የጣዖት አይነቶች ያሉ ቢሆንም በአምስት ዋና  ክፍሎች ይከፈላሉ። እነዚህም የጣዖት አውራዎች ተብለው ይጠራሉ።

1ኛ ሰዎች ከአሏህ ውጭ ያሉ ነገሮችን እንዲያመልኩ የሚጣራው ሸይጧን ነው። ለዚህም ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

**=<({አል-ቁርአን 36:60})>=**

**{60} የአደም ልጆች ሆይ! ሸይጧንን እንዳታመልኩ አላዘዝኳችሁምን? በእርግጥ እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነው።**

2 የአሏህን ህግጋት የቀየሩ ጨካኝና ጭቋኝ አንባገነን ገዥዎች! ለዚህ ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

=<({አል-ቁርአን 4:60})>=

أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ يَزۡعُمُونَ أَنَّهُمۡ ءَامَنُواْ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبۡلِكَ يُرِيدُونَ أَن يَتَحَاكَمُوٓاْ إِلَى ٱلطَّٰغُوتِ وَقَدۡ أُمِرُوٓاْ أَن يَكۡفُرُواْ بِهِۦۖ وَيُرِيدُ ٱلشَّيۡطَٰنُ أَن يُضِلَّهُمۡ ضَلَٰلَۢا بَعِيدٗا

**{60} እነዚያ ወደ አንተ በተላከው እና ከአንተ በፊት በተላከው አምነናል የሚሉትን አላየህምን? በእርሱ እንዲክዱ ከታዘዙ ብኋላ ለፍርድ ወደ ጧኡት (ወደ ውሸት ዳኞች) መሄድ ይሻሉ። ነገርግን ሸይጧን ሊያጠማቸው ይሻል።**

3ኛ አሏህ ከገለፀው ውጭ በሆነ የሚዳኝ! ለዚህም ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

=<({አል-ቁርአን 5:44})>=

**{44} አሏህ ባወረደው(በገልፀው) የማይዳኙ እነዚያ እነሱ ከሃዲያኖች ናቸው።**

4ኛ ከአሏህ ተነጥሎ እሩቅን አዋቂ ነው ተብሎ የሚታመንበት ወይም ሩቅን አውቃለሁ የሚል! ለዚህ ማስረጃ ተከታዩ የአሏህ ንግግር ነው።

=<({አል-ቁርአን አልጅን 26-27})>=

عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ فَلَا يُظۡهِرُ عَلَىٰ غَيۡبِهِۦٓ أَحَدًا ( ٢٦ ) إِلَّا مَنِ ٱرۡتَضَىٰ مِن رَّسُولٖ فَإِنَّهُۥ يَسۡلُكُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَمِنۡ خَلۡفِهِۦ رَصَدٗا ( ٢٧ )

{26} እርሱ(አሏህ) ሩቅን ሚስጥር አዋቂ ነው። በሚስጥሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም።

{27} ከመልዕክተኛው ለወደደው ቢሆን እንጅ ለሌላው አይገልፅም። እርሱም ከስተፊለፊትም ከስተኋላም ጠባቂዎችን ያደርግለታል።

=<({አል-ቁርአን አንአም 6:59})>=

وَعِندَهُۥ مَفَاتِحُ ٱلۡغَيۡبِ لَا يَعۡلَمُهَآ إِلَّا هُوَۚ وَيَعۡلَمُ مَا فِى ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۚ وَمَا تَسۡقُطُ

مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعۡلَمُهَا وَلَا حَبَّةٍ فِى ظُلُمَٰتِ ٱلۡأَرۡضِ وَلَا رَطۡبٍ

وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِى كِتَٰبٍ مُّبِينٍ

{59} የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው። ከእሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባህር ያለውንም ሁሉ ያውቃል። አንዲትም ቅጠል አትረግፍም እርሱ የሚያውቃት ቢሆን እንጅ። ቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልፅ በሆነው መፅሐፍ ውስጥ የተመዘገበ ቢሆን እንጅ።

5ኛ ከአሏህ ውጭ የሚመለክ እና ሲመለክ ውዴታ ያለው! ለዚህ ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

=<({አል-ቁርአን አቢያ 29})>=

وَمَن يَقُلۡ مِنۡهُمۡ إِنِّىٓ إِلَٰهٌ مِّن دُونِهِۦ فَذَٰلِكَ نَجۡزِيهِ جَهَنَّمَۚ كَذَٰلِكَ نَجۡزِى

ٱلظَّٰلِمِينَ ۝

{29} ከእነሱም መካከል እኔ ከእሱ ሌላ አምላክ ነኝ አለ። እናም ይህን በጀሃነም እሳት እንመነዳዋለን። እንደዚሁ በዳዮችን እንመነዳዋለን።

# ማብራሪያ

ፀሐፊዊ አሏህ ይዘንላቸውና ጣዖት የሚለው ቃል አንድን ግለሰብ ወይም ሌላ ፍጡር ብቻ የሚያመላክትና የሚገልፅ ሳይሆን ሰፋ ያለ ሃሳብ እንደሆነ አውስተው በርካታ አይነቶችም እንዳሉት ገልፀዋል። በእርግጥ ከአሏህ ውጭ የሚመለክ ወይም ከአሏህ ውጭ የሚከተሉት ወይም ደግሞ አሏህና መልዕክተኛውን አለመታዘዝ በሆነ ጉዳይ ላይ ሰዎች የሚታዘዙት እና የሚከተሉት ያ ጣኦት ነው። በዚህ ባህሪ የሚገልፁ የጣኦት አይነቶች ብዙ ናቸው። ነገርግን ትልልቆቹ የጣኦት አውራ ወይም መሪዎች በአምስት ይከፈላሉ።

## 1ኛ ሸይጧን

ሰዎች ከአሏህ ውጭ ያሉ ነገሮችን እንዲገዙ ከሚጣሩ ሁሉ የጣኦት አውራ ነው። እሱም ከአሏህ ውጭ የሆነንን ነገር ሲያመልኩ ይደሰታል። ምክኒያቱም ጥሪ የሚያደርገው ወደዚህ ነውና። በአሁኑ ሰአትም አለም ላይ ያሉ ተዋቂናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችም ሆኑ ቲፎዞዎቻቸው አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት 666 የሚባልን ሸይጧን በመገዛት ላይ ይገኛሉ። አሏህም እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 36:60})>=**

**{60} የአደም ልጆች ሆይ! ሸይጧንን እንዳታመልኩ አላዘዝኳችሁምን? በእርግጥ እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነው።**

ሆኖም ቁርአን ሸይጧንን እንደሚያመልኩት በግልፅ ገልፃል። ምክኒያቱም ከአሏህ ይልቅ እሱን መታዘዛቸው እና መከተላቸው ነበር።

**2 ሁለተኛው የጣኦቶች አውራ የሆነው የአሏህን ህግ የቀየረ አንባገነን መሪ ነው።** ልክ አይሁዳውያኖች እንዳረጉት ማለት ነው።

ይህን የሚያደርገው አንድም የአሏህን ህግ ለማንቋሸሽ ነው ወይም ከአሏህ ህግ በላይ በተሻለ ሰዎች በፍትሃዊነት የሚተዳደሩበት ህግ አለ ብሎ በማሰብ ነው። ወይም ደግሞ የአሏህን ህግ የቀየረውን ገዥ ሸይጧን ተቆጣጥሮታል ማለት ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአሏህ ንግግር ነው።

**=<({አል-ቁርአን 4:60})>=**

**أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ يَزۡعُمُونَ أَنَّهُمۡ ءَامَنُواْ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبۡلِكَ يُرِيدُونَ أَن يَتَحَاكَمُوٓاْ إِلَى ٱلطَّٰغُوتِ وَقَدۡ أُمِرُوٓاْ أَن يَكۡفُرُواْ بِهِۦۖ وَيُرِيدُ ٱلشَّيۡطَٰنُ أَن يُضِلَّهُمۡ ضَلَٰلَۢا بَعِيدٗا**

**{60} እነዚያ ወደ አንተ በተላከው እና ከአንተ በፊት በተላከው አምነናል የሚሉትን አላየህምን? በእርሱ እንዲክዱ ከታዘዙ ቡኋላ ለፍርድ ወደ ጧኡት (ወደ ውሸት ዳኞች) መሄድ ይሻሉ። ነገርግን ሸይጧን ሊያጠማቸው ይሻል።**

አሏህ ሁኔታቸውን እንደገለፀው እምነት አለን ብለው ያወጁ ቢሆንም ውድቅ እንዳደረገባቸውና ውሸታሞች እንደሆኑ ገልፃል። ለዚህም ምክኒያቱ ከአሏህ ፍርድ ውጭ ሌላን በመፈለጋቸውና ከአሏህ ህግ በማፈግፈጋቸው ነበር። ይህ በጣኦት እንዲክዱና ከነሱም ፍርድ እንዳይፈልጉ ከታዘዙ ቡኋላ ነበር። ነገርግን ሸይጧን

አሸንፏቸው ከአሏህ መንገድ አጠመማቸው።

ማንኛውም የአሏህን ህግ በሊበራሊዝም ፣ በዲሞክራሲ ፣ በሶሻሊዝም ፣ በኮሚንዝም ፣ በፊውዳሊዝም የቀየረ መሪ የጣኦቶች አውራ ነው። እንዲሁም የህገመንግስት የበላይነት የሚሉ መሪዎች እና ደቀመዛሙርቶቻቸው በዚህ ስር ይጠቃለላሉ።

**3 ሶስተኛው የጣኦት አውራ አሏህ ከገለፀው ነገር ውጭ በሆነ ህግ የሚያስተዳድርና የሚዳኝ ነው።** አሏሁ አዘወጀል እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 5:44})>=**

**{44} አሏህ ባወረደው(በገልፀው) የማይዳኙ እነዚያ እነሱ ከሃዲያኖች ናቸው።**

ይህ ዳኛም ሆነ ንጉስ ወይም ፕሬዝዳንት ወይም ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር ወዘተ አንድ ናቸው። እናም አሏህ ከገለፀው ውጭ በሆነ ነገር የዳኘ እርሱ የጣኦት አውራ ነው።

**4 ከአምስቶቹ የጣኦት አውራዎች አራተኛው ከአሏህ ውጭ የሆነ የሩቅ ሚስጥርን ያውቃል ተብሎ የሚታመንበት፤ መይም የሩቅ ሚስጥር አውቃለሁ የሚል ነው።** ምክኒያቱም ከፍጡራኖቹ ተለይቶ የሩቅ ሚስጥ እውቀት ያለው ወይም የሩቅ ሚስጥርን የሚያውቀው አሏህ ብቻ ነውና። አሏህም እንዲህ ይላል፡-

=<({አል-ቁርአን አልጅን 26-27})>=

عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ فَلَا يُظۡهِرُ عَلَىٰ غَيۡبِهِۦٓ أَحَدًا ( ٢٦ ) إِلَّا مَنِ ٱرۡتَضَىٰ مِن
رَّسُولٖ فَإِنَّهُۥ يَسۡلُكُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَمِنۡ خَلۡفِهِۦ رَصَدٗا ( ٢٧ )

{26} እርሱ(አሏህ) ሩቅን ሚስጥር አዋቂ ነው። በሚስጥሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም።

{27} ከመልዕክተኛው ለወደደው ቢሆን እንጅ ለሌላው አይገልፅም። እርሱም ከስተፊለፊትም ከስተኋላም ጠባቂዎችን ያደርግለታል።

=<({አል-ቁርአን አንአም 6:59})>=

وَعِندَهُۥ مَفَاتِحُ ٱلۡغَيۡبِ لَا يَعۡلَمُهَآ إِلَّا هُوَۚ وَيَعۡلَمُ مَا فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۚ وَمَا تَسۡقُطُ
مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعۡلَمُهَا وَلَا حَبَّةٖ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡأَرۡضِ وَلَا رَطۡبٖ
وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ

{59} የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው። ከእሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባህር ያለውንም ሁሉ ያውቃል። አንዲትም ቅጠል አትረግፍም እርሱ የሚያውቃት ቢሆን እንጅ። ቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልፅ በሆነው መፅሐፍ ውስጥ የተመዘገበ ቢሆን እንጅ።

በሩቅ ሚስጥር እውቀት የሚገለፀው አሏህ ብቻ ነው። ይህንንም የማወቅ ብቃት ማንም የለውም በፈቃዱ ቢሆን እንጅ። ፍጡራኖችም የሩቅ ሚስጥር እውቀት

ወይም ወደ ፊት ምን እንደ ሚከሰት ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። ከአሏህ ውጭ ለራሱ እኔ የሩቅ ሚስጥር እውቀት አለኝ ብሎ ያለም ሆነ የሩቅ ሚስጥር አለው ብሎ ያለ በእርግጥ እሱ በአሏህ ክዷል። ምክኒያቱም እሱ ብቻ ባለው ሙብት ላይ ሌላ ባላንጣን አበጅቷልና ነው።

**5 አምስተኛውና የመጨረሻው የጣኦት አውራ ወይም መሪ ከአሏህ ውጭ የሚመለክ ነገር** ሲሆን ብዙ የጣኦት አይነቶችም በዚህ ስር ሊካተቱ ይችላል። ለዚህ ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

**=<(﴾አል-ቁርአን አቢያ 29﴿)>=**

**وَمَن يَقُلْ مِنْهُمْ إِنِّىٓ إِلَٰهٌ مِّن دُونِهِۦ فَذَٰلِكَ نَجْزِيهِ جَهَنَّمَ ۚ كَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلظَّٰلِمِينَ**

**﴾29﴿ ከእነሱም መካከል እኔ ከእርሱ ሌላ አምላክ ነኝ አለ። እናም ይህን በጀሃነም እሳት እንመነዳዋለን። እንደዚሁ በዳዮችን እንመነዳዋለን።**

እናም ይህ ልክ ፊርአውን እንዳደረገው ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ የሚያደርግ እና እራሱን ጌታ ያደረገን ሰው ሁሉ ያጠቃልላል። እነዚህ የጣኦት አውራዎች ተብለው ይገለፁ እንጅ በዚች ፅሁፍ ያልተካተቱ በርካታ የጣኦት አይነቶች አሉ።

# ማጠቃለያ

1. ጧኡት_ ከአሏህ ውጭ የሚመለክ ማንኛውም ነገር

2. የጧኡት አይነቶች ብዙ ናቸው ነገርግን ወሳኝ የሆኑት የጣኡት አይነቶች አምስት ናቸው።

# ጥያቄና መልስ

1. የጣኡት ትርጉም የተወሰነ ነው ወይስ ሰፋ ያለ?

2. ወሳኝ የሆኑት የጣኡት አውራዎች እነማን ናቸው?

3. ሸይጧን አንዱ የጣኡት አውራ ስለመሆኑ ማስረጃው ምንድነው?

4. የሩቅን ሚስጥር አውቃለሁ ብሎ በሚያምን ሰው ላይ ፍርዱ ምንድነው? ማስረጃህን ግለፅ

# ክፍል አራት

## በጣዖት መካድ ለእምነት መስተካከል መሰረት ነው።

እወቅ! የሰው ልጅ ጣዖቶችን ውድቅ እስካላደረገና በጣዖት እስካልካደ ድረስ በፍፁም በአሏህ አማኝ አይሆንም። ለዚህ ማስረጃው የአሏህ ንግግር ነው።

**=<({አል-ቁርአን 2:256})>=**

لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِن
ۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ

**{256} በሃይማኖት ማስገደድ የለም። በእርግጥም ቀጥተኛው መንገድ ከጠማማው መንገድ ተገለጠ። በጣዖትም የሚክድና በአሏህ የሚያምን ሰው ለእሱ የማትበጠስ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ። አሏህም ሰሚ አዋቂ ነው።**

እዚህ ላይ ቀጥተኛው መንገድ የሚያመለክተው የሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ሃይማኖት ሲሆን ጠማማው መንገድ ደግሞ የአቡ ጀህል ሃይማኖት ነው። ጠንካራው የማይበጠሰው ዘለበት የላኢላሃ ኢለሏህን የምስክርነት ቃል ሲሆን ይህ የምስክርነት ቃልም ውድቅ የማድረግን እና የማረጋገጥን መርህ ይዟል። ይህም ከአሏህ ውጭ ላሉ ነገሮች ተብለው የሚሰሩ የኢባዳ አይነቶችን ውድቅ ማድረግ ሲሆን ለአሏህ ብቻ ተብለው የሚሰሩ የአምልኮት ተግባራትን ማረጋገጥ ነው።

# ማብራሪያ

**<u>የቃላት ፍች</u>**

- ኢስተምሰከ_ የሚያዝ
- ኢንፊሷም_ የማይሰበር ፣ የማይለያይ
- ገይ_ ጠማማ መንገድ ፣ ጥመት ፣ ማፈንገጥ

አንድ ሰው መጀመሪያ በጣኦት እስካልካደ ድረስ በአሏህ ላይ እምነት ሊኖረው አይችልም። ምክኒያቱም ኢማን(እምነት) እና ሽርክ(ማጋራት) ወይም ክህደት ተቃራኒና ተፃራሪ በመሆናቸው አንድ ላይ አብረው በአንድ ልብ ውስጥ መቀመጥ አይችሉምና። በመጀመሪያ ከአሏህ ውጭ ላሉ የሚደረጉ የእምልኮት ተግባራትን ካስወገዱ ብኋላ የአምልኮት ተግባራትን በመሉ ለአሏህ ብቻ ማድረግ ይኖርበታል። አሏህም እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 2:256})>=**

لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ
بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ

**{256} በሃይማኖት ማስገደድ የለም። በእርግጥም ቀጥተኛው መንገድ ከጠማማው መንገድ ተገለጠ። በጣዖትም የሚክድና በአሏህ የሚያምን ሰው ለእሱ የማትበጠስ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ። አሏህም ሰሚ አዋቂ ነው።**

እናም አሏህ በጣዖት መካድ ሲል ከጀመረ ቡኋላ በአሏህ ማመን አለ። በማስከተልም ለተናገረውም ነገር ማረጋገጫውን እና ማብራሪያውን ሲያስቀምጥ ሩሽድ (መመሪያ ፣ ቀጥተኛ መንገድ) ሲል ገለፀ። ይህ ማለት የሙሐመድ ሃይማኖት ሲሆን ፣ የንፁህ አሃዳዊነት እምነት ፣ አሏህን በኢባዳ መነጠል እና ሃይማኖትን ለእሱ ብቻ ማድረግ ነው። ገአይ (ጥመት ፣ ጠማማ መንገድ) ማለት የአቡ ጀህል እምነት  ሲሆን ከአሏህ ጋር ባላንጣ ማበጀት ፣ ከአሏህ ውጭ ኢባዳን ለሌላ እንዲያደርጉ ማመላከትና በአሏህ ላይ ማሻረክ ነው።

ኡስወቱል ኡስቃ (የማይበጠስ ዘለበት) ማለት የላኢላሃ ኢለሏህ መርህ ሲሆን ውድቅ ማድረግን ፣ መቃረንን እና ማረጋገጥን የሚገልፅ ነው። ላኢላሃ የሚለው ከአሏህ ውጭ የሚመለኩ ነገሮች ይቃረናል ወይም ውድቅ ያደርጋል። ምክኒያቱም የመመለክ መብቱም ሆነ በዚህ ፍጥረተ አለም ላይ የመቆጣጠር ሃይልም ብቃቱም የላቸውምና። ኢለሏህ የሚለው የአምልኮት ተግባራትን ለአሏህ ማረጋገጥ ነው። ምክኒያቱም የአምልኮት ተግባራቶች ሁሉ የሚገቡት ለአሏህ ነውና። ምክኒያቱም የመፍጠር ፣ የባለቤትነት እና በፍጥረተ አለም ላይ የማስተናበር ባህሪ ያለው እሱና እሱ ብቻ ነውና።

## ማጠቃለያ

1. በጣኦት መካድ የኢማን መስተካከል መሰረት ነው።
2. ሩሽድ ቀጥተኛ መንገድ ማለት ተውሂድ ሲሆን ገአይ ጠማማ መንገድ ማለት ደግሞ ሽርክ ነው።
3. ላኢላሃ ኢለሏህ የሚለው የምስክርነት ቃል የመቃረን ፣ ውድቅ የማድረግ እና የማረጋገጥ መርሆዎችን ይዟል።

## ጥያቄና መልስ

1. የትኛው ነው የሚቀድመው በጣዖት መካድ ወይስ በአሏህ ማመን?
2. የሚከተሉት ቃላት ትርጉማቸው ምንድነው? ሀ) ሩሽድ ለ) ገአይ ሐ) ኡርወቱል ኡስቃ
3. ላኢላሃ ኢለሏህ የሚለው የምስክርነት ቃል ውድቅ የማድረግና የማረጋገጥ መርህን አካቷል ሲባል ምን ማለት ነው?

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙሏህ ኸይረን ከሲረን!